# ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽሕፈት ቤት

# የተሰጠ መግለጫ

## የተዛባና ወገናዊ የምርጫ ታዛቢ ሪፖርት

## ለኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ዕድገት የሚፈይደው ነገር የለም

የኢትዮጵያ መንግሥትና ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የተካሄደውን ሦስተኛውን የሕዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ፍፁም ነፃና ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ በርካታ አዎንታዊ እርምጃዎችን ሲወስዱ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት እንዲከታተሉ የተጋበዙበት የሚጠቀስ ሲሆን ጥሪ የተደረገላቸው አለም አቀፍ ታዛቢዎች ምርጫው ከመካሄዱ ከወራት በፊት በመግባት የቅድመ ምርጫ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ሲከታተሉ ቆይተዋል፡፡ ከዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ውስጥ የአውሮፓ ሕብረት፣ የካርተር ማዕከል፣ የአፍሪካ ሕብረትና የአረብ ሊግ በተቋም ደረጃ የተጋበዙ ሲሆን ሌሎች በርካታ የአውሮፓ፣ የሰሜን አሜሪካ፣ የአፍሪካና የኤሲያ ሀገራት በተወካዮቻቸው አማካኝነት ምርጫውን ታዝበዋል፡፡ አብዛኞቹ የምርጫ ታዛቢ ቡድኖች ምርጫው እንደተጠናቀቀ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርታቸውን ያቀረቡ ሲሆን በአቀራረብ ቢለያዩም በአመዛኙ ከምርጫው በፊትና በምርጫ ቀን የነበረው ሁኔታ ሕዝቡ ፍላጎቱን ያለምንም ተፅዕኖ በነፃ የገለፀበት፣ ከምን ጊዜውም የተሻለ ዝግጅትና አደረጃጀት የነበረበትና ለሌሎች ሀገራትም በአርአያነት ሊጠቀስ የሚችል ምርጫ እንደነበረ መስክረዋል፡፡

ምንም እንኳን አለም አቀፍ ታዛቢዎች ያሰማራቸው ታዛቢ ቡድኖች ከአገሪቱ የቆዳ ስፋትና የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት አንፃር ሲታዩ አነስተኛ ቢሆኑም የታዛቢ ቡድኖቹ በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች የሚያቀርቡት ግምገማ የምርጫ ሂደቱን ጠንካራና ደካማ ጎን በማሳየት ለቀጣዩ የምርጫ አፈፃፀም ገንቢ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል እምነት በመንግሥትም ሆነ በምርጫ ቦርድ ተይዞ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የአውሮፓ

ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ነሐሴ 19 ቀን 1997 ዓ.ም. ያወጣው ሪፖርት የምርጫ ሥርዓቱን ከማጠናከር ይልቅ አፍራሽነቱ አመዝኖ ተገኝቷል፡፡ የሕብረቱ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ተጠሪ ሚስዝ አና ጎሜዝ ይፋ ባደረጉት በዚሁ ሪፖርት የቀረቡት ግምገማዎች እውነታን ሆን ብለው የሚያጣምሙና የአንድን ወገን ፍላጎት ብቻ የሚያንፀባርቁ እንዲሁም እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ሆኖ ስላገኛቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሪፖርቱ ላይ ያለውን አስተያየት ለመስጠት ይገደዳል፡፡

ታዛቢ ቡድኑ ባወጣው ሪፖርት የምርጫ ቦርድ ከፓርቲዎች የቀረቡለትን አቤቱታዎች ለማጣራት ዝርዝር የአሠራር ደንቦችን ማውጣቱንና ይህም ፓርቲዎች ያላቸውን ቅሬታ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ዕድል እንደሰጣቸው ጠቅሷል፡፡ ይህ አሠራርም በጎ ጅምር እንደሆነና በሂደቱ የተገኙ ልምዶችን በማካተት ለወደፊቱ ሊጎለበት እንደሚገባው ገልጿል፡፡ ከዚህም ባሻገር ፓርቲዎቹ በተፈጠረላቸው መድረክ አማካኝነት ኃሣባቸውን እንዲገልፁ መደረጉ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ የሆነ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑንም አብራርቷል፡፡ የአቤቱታ አጣሪ ቡድኖችም በአጠቃላይ ሲታይ በወጣላቸው የአሠራር ደንብና መመሪያ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን አመልክቷል፡፡

እውነታው ይህ ሆኖ እያለ የቡድኑ ኃላፊ ከማጣራት ሂደቱ ጋር ግንኙነት በሌለው እና በማይመለከታቸው የሀገሪቱ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠታቸው የታዛቢ ቡድኑ ሪፖርት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰኔ 3 ቀን 197 ዓ.ም. በፈረሙት ስምምነት መሠረት ወደ አቤቱታ ማጣራት ሥራው ለመግባት በሰኔ 1ዱ ሁከት ምክንያት የታሰሩ አባሎቻችን ይፈቱልን የሚል ተቀባይነት የሌለው ቅድመ ሁኔታ አስቀምጠው እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ይህም ቅድመ ሁኔታ በራሱ በአውሮፓ ህብረት ውድቅ መደረጉ ይታወሳል፡፡ በሌላ በኩል በአቤቱታ ማጣራት ሂደቱ እንደታየው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረቧቸው ምስክሮች ለምን ጉዳይ ምስክርነት እንደተጠሩ እንኳ የማያውቁ ምስክርነታቸውን የሰጡትም ቢሆን ፓርቲዎቹ ከሚያቀርቡት ክስ በተቃራኒው መመስከራቸው ታዛቢዎቹ ባሉበት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ለምስክርነት ተፈልጎ እንዳይቀርብ የተደረገም ሆነ ለተቃዋሚ ፓርቲ በመመስከሩ ችግር የደረሰበት ምስክር ወይም የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ስለመኖሩ ለቦርዱ የደረሰው አንዳችም ሪፖርት የለም፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ደረሰን በተባለ መረጃ ብቻ ተመስርቶ የምስክሮችና የፓርቲ

አመራሮች ሰብዓዊ መብት ተጥሷል የሚል ሪፖርት ማቅረብ ኃላፊነት ከሚሰማው ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢ የሚጠበቅ አይደለም፡፡

ሚስዝ ጎሜዝ ከዚህም አልፈው ከኃላፊነት ክልላቸው ፍፁም በወጣ መልኩ ተቃዋሚዎችን በመጥቀስ በሀገሪቱ በዳኝነትና አስፈፃሚ አካሉ መካከል ግልፅ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል የለም እስከማለት ደርሰዋል፡፡ ኃላፊዋ በማይመለከታቸው የሀገራችን የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓት ውስጥ ገብተው አስተያየት መስጠታቸው ሕዝቡ በሀገሪቱ የፍትሕና የዲሞክራሲ ተቋማት ላይ እምነት እንዳይኖረው አፍራሽ አቋሞችን ለሚያራምዱ ኃይሎች በመሳሪያነት እንዳያገለግሉ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ሪፖርት እንዳመለከተው የሕብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው በርካታ አጋጣሚዎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረቡት ማስረጃ ደካማና እርስ በእርሱ የሚጋጭ እንደነበር መታዘባቸውን ተናግረዋል፡፡ በሌላም በኩል ኢሕአዴግ ያቀረባቸው ክሶች በአጥጋቢ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውንና አስረጂዎቻቸውም ሆኑ ምስክሮቻቸው በሚገባ የተዘጋጁ መሆናቸውን አልካደም፡፡ ይሁን እንጂ ተቃዋሚዎች ጠንካራ መረጃ ባቀረቡበት ሁኔታ አቤቱታቸው ውድቅ መደረጉን ለአብነትም የሻሸመኔ 1 የምርጫ ክልልን ይጠቅሳል፡፡ በሻሸመኔ 1 የምርጫ ክልል የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት (ኢዴኃህ) ዕጩዎች አቀረቡ የተባሉት የውጤት መተማመኛ ሰነድ ለአጣሪ ቡድኑ ቀርቦ ሲመረመር አብዛኛው በምርጫ ክልሉ ያልተሰጠና ተመሳስሎ የተሰራ ቀሪው ደግሞ ስርዝ ድልዝ የበዛበት ሆኖ በመገኘቱ አጣሪ ቡድኑ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የዚህ አይነቱን የተጭበረበረ ሰነድ ተቀብላችሁ ፍረዱ ማለት ሕገወጥነትን ከማበረታታት ያለፈ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡

ሚስዝ ጎሜዝ በሪፖርታቸው በሰሜን ሸዋ ዞን መራኛ የምርጫ ክልል ውዱ ደለለኝ የተባለ የቅንጅት ምስክር የምስክርነት ቃሉን ለአጣሪ ቡድኑ ሰጥቶ ከሄደ ከ5 ቀናት በኋላ መገደሉን ጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል የጉዳዩ ባለቤት ቅንጅት በስም ተጠቃሹ ሟች ለምስክርነት ከመቅረቡ በፊት እንደተገደለበት ይናገራል፡፡ በስፍራው የተገኘው የአጣሪ ቡድን ግለሰቡ በቅንጅት ምስክርነት እንዳልተጠራና የአሟሟቱም ጉዳይ ከምርጫ ማጣራት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ቁም ነገሩ ግን የሕብረቱ የታዛቢ ቡድን ኃላፊ ከተቃዋሚዎች የተነገራቸውን በራሳቸው

ታዛቢዎች አማካኝነት ለማጣራት ይቅርና ተቃዋሚው የሚለውን እንኳ በአግባቡ ለማስተጋባት አለመቻላቸው ነው፡፡

የታዛቢ ቡድኑ የምርጫ ማጣራት መመሪያው አተገባበር በአንዳንድ ቦታዎች ወጥነት እንደሚጎድለው ገልጿል፡፡ ለዚህም እንደ ማስረጃ ያቀረበው በምስራቅ ሸዋ ዞን የሕብረቱ ተወካይ አጣሪ ቡድኑን ከመቀላቀላቸው በፊት የ3 የምርጫ ክልሎችን ጉዳይ በ4 ቀናት መጠናቀቁ ሲሆን የሕብረቱ ተወካዮች ቡድኑን ከተቀላቀሉ በኋላ ግን ለአንድ የምርጫ ክልል ቢያንስ ሦስት ቀን መውሰዱን ይጠቅሳል፡፡ በምስራቅ ሸዋ ዞን አድአ 1 እና አድአ 2 የምርጫ ክልሎች አቤቱታ ያቀረበው ኢዴኃህ ሲሆን የክሱ ይዘትም ታዛቢዎቹ በታጣቂዎች ተባረዋል፣ ሕዝብ በኃይል እንዳይመርጥ ተደርጓል የሚሉ ይገኙበታል፡፡ ኢዴኃህ እነዚህን ቅሬታዎች ያቀረበው በሁለቱም የምርጫ ክልሎች ያሸነፈው ኢሕአዴግ ነው በሚል ታሳቢ ሲሆን በአንፃሩ ግን በሁለቱም የምርጫ ክልሎች ያሸነፈው ቅንጅት ነበር፡፡ አሸናፊው ቅንጅት መሆኑን የተረዳው ኢዴኃህ ወዲያውኑ ክሴን አንስቻለሁ በማለቱ አጣሪ ቡድኑ ወደ ሌሎች የምርጫ ክልሎች ተንቀሳቅሷል፡፡ ይህ ጉዳይ የተለገፀላቸው የአውሮፓ ሕብረት ታዛቢዎች አጣሪ ቡድኑን ለመተቸት ከመጣደፍ ይልቅ ኢዴኃህ አቅርቦት ስለነበረው አሳፋሪ የፈጠራ ክስ ሊነግሩን በተገባ ነበር፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረቧቸው አብዛኞቹ ክሶች ውድቅ መደረጋቸውን በአንፃሩ ገዥው ፓርቲ ያቀረባቸው አቤቱታዎች ተቀባይነት ማግኘታቸውን እና ጎሜዝ በሪፖርታቸው ገልፀዋል፡፡ ውሣኔው የዚህ ዓይነቱን አዝማሚያ ሊይዝ የቻለው በቀረቡት መከራከሪያዎች ጥንካሬና ድክመት መሠረት ሊሆን እንደሚችል የጠቆሙት ኃላፊዋ ጠንካራ መረጃ የቀረበባቸው ክሶችም ቢሆን አሳማኝ ባልሆነ ሁኔታ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም ብለዋል፡፡ የታዛቢ ቡድኑ ኃላፊ በአንድ በኩል አጣሪ ቡድኑ በአጠቃላይ በተቀመጠለት መመሪያ መሠረት ሥራውን ማከናወኑን እየነገሩን በሌላ በኩል ውሣኔዎቹ አሳማኝ አልነበሩም ይሉናል፡፡ ቁም ነገሩ ግን የአጣሪ ቡድኖቹ የውሣኔ ኃሣባቸውን የሚሰጡት ታዛቢዎች ስላመኑበትና ስላላመኑበት ሳይሆን የቀረበላቸውን ክስ የሚደግፍ አሳማኝ ማስረጃ መኖሩን በመመዘን መሆኑ ነው፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ሪፖርት ከየትኛውም ወገን ያልተሰጡ የሀሰት ክሶችንም ያካተተ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሪፖርቱ በሲዳማ ዞን ሀገረ ሰላም የምርጫ ክልል ኢሕአዴግ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዕጩነት ያቀረባቸው ባለሥልጣን

በግንቦት 7ቱ ምርጫ ያጡትን ወንበር ለማስመለስ ዳግም ምርጫ ተካሂዷል ይላል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በሀገረ ሰላም የምርጫ ክልል በተፈጠረው የምርጫ ግድፈት ምክንያት ቆጠራው ባለመጠናቀቁ አሸናፊው በጊዜያዊ ውጤትም ቢሆን አልተገለፀም፡፡ እና ጎሜዝ በሀገረሰላም ኢሕአዴግ ተሸንፎ ነበር የሚለውን የፈጠራ ሪፖርታቸውን ከየት እንዳመጡት የሚያውቁት ምናልባትም እርሳቸው ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ዳግም ምርጫው የተካሄደው ባለሥልጣኑ ያጡትን ወንበር ለማስመለስ ነው ማለታቸው የአቤቱታ አጣሪ ቡድኑና ቦርዱ ያሳለፉቸውን ውሳኔዎች እውቅና ላለመስጠት መፈለጋቸውን በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡

የሕብረቱ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ኃላፊ የማጣራት ሂደቱ አለም አቀፍ ዲሞክራሲያዊ መስፈርትን ያሟላ አልነበረም ላሉት ግምገማ እንደ ማስረጃ ያቀረቡት የሰኔ አንዱን ሁከት ተከትሎ ተፈፀመ ያሉት ዜጎች በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠላቸው የሰብዓዊ መብቶች መጣስ ነው፡፡ ይሁንና እርሳቸው በጠቀሱት ሕገ መንግሥት ውስጥ የመንግሥት ሥልጣን በዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንጂ በአመፅና በሁከት እንደማይያዝና መንግሥት ሕገወጥነትንና ሥርዓት አልበኝነትን የመከላከልና ሕገመንግሥቱን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበት ሳይጠቅሱ ማለፋቸው የሪፖርታቸውን ሚዛናዊነት ጥርጣሬ ውስጥ ያስገባ ሆኗል፡፡ ሚስዝ ጎሜዝ ከዚህም ባሻገር ከግንቦት 7ቱ ምርጫ በኋላ የሀገሪቱ ፓርላማ አዳዲስ አዋጆችን ማውጣቱ ምርጫውን አለም አቀፍ መስፈርት ያሟላ አያደርገውም ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፓርላማ የሀገሪቱ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሉዓላዊነት መገለጫ ሲሆን በዚህች ሀገር ህግ የማውጣት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውም ለዚሁ ፓርላማ ነው፡፡ ፓርላማው በሕግ የተደነገገ የሥራ ጊዜ ያለው ሲሆን በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥም በአሰራር ደንቡ መሠረት ሕገ መንግሥቱን መሠረት ያደረጉ ማናቸውንም ሕጎች የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡ እና ጎሜዝ እና እርሳቸው የሚመሩት የታዛቢ ቡድን ይህን አሠራር መተቸታቸው የኃላፊነት ክልላቸውን በሚገባ ያልተረዱ መሆናቸውን ከማሳየቱም ባሻገር የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚጻረር ነው፡፡ ይህ አድራጎታቸውም የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የአውሮፓ ሕብረት ወደ ኢትዮጵያ የላከውን የምርጫ ታዛቢ ቡድን ማንነት ክፉኛ እንዲጠራጠር አድርጎታል፡፡

የዳግም ምርጫው ሂደት 64( ጥሩ እና 24( በጣም ጥሩ በሚለው ደረጃ መመደቡ፣ ድምፅ አሰጣጡ ሰላማዊና ሥርዓት ባለው ሁኔታ መካሄዱና የምርጫ ሕጉ በአግባቡ ተግባር ላይ መዋሉን በተመለከተ የሕብረቱ ታዛቢ ቡድን ያነሳቸውን ነጥቦች ቦርዱ

በአመዛኙ ይጋራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በደካማ ጎንነት የተነሱት በተለይ ሁለት ነጥቦች ችግር ያለባቸው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከነዚህም አንደኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች በምርጫ ጣቢያዎች በበቂ አለመገኘት የሚለው ሲሆን ቦርዱ ለፓርቲዎች ታዛቢዎቻቸውን እንዲልኩ ከማሳወቅ ባለፈ የማስገደድ ሥልጣን ስለሌለው መተቸት ካለባቸው ተወካዮቻቸውን ያላስቀመጡ ፓርቲዎች እንጂ ቦርዱ መሆን የለበትም፡፡ የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ቁጥር አነስተኛ ነበር ለተባለውም ቦርዱ በመገናኛ ብዙሃን በተደጋጋሚ ምርጫውን ለመታዘብ ለሚፈልጉ የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ፈቃድ መውሰድ እንደሚችሉ በገለፀው መሠረት ሂደቱን ለመታዘብ የፈለጉ ድርጅቶች ፈቃድ ተሰጥቷቸው ዳግም ምርጫውን ተከታትለዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ታዛቢዎቹ በአቅም ማነስና በራሳቸው ልዩ ልዩ ችግሮች ምክንያት መሳተፍ ካልቻሉ ችግሩ የታዛቢዎች እንጂ የምርጫ ሂደቱ አካል አለመሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግሥትና ምርጫ ቦርድ የአውሮፓ ሕብረትን ጨምሮ የውጭ ታዛቢዎችን ሲጋብዙ ለምርጫው ሂደትና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ በሚል ተስፋ ነበር፡፡ ይሁንና የሕብረቱ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ሪፖርት በአብዛኛው ተዓማኒነት የሚጎድለው፣ እርስ በእርሱ የሚጣረስና ግልፅ ወገንተኝነት የተንፀባረቀበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሚስዝ አና ጎሜዝ የቀረበው የተዛባና ሚዛናዊነት የጎደለው ሪፖርት የታዛቢ ቡድኑን ማንነት በግልፅ ከማሳየት ባለፈ ታሪካዊነቱ በኢትዮጵያ ሕዝቦች እና ሃቀኛ ታዛቢዎች በተመሰከረለት የግንቦት 7ቱ ምርጫ ሂደትና ውጤት ሆነ በቦርዱ አሰራር ላይ የሚያሳድረው አንዳችም ተጽእኖ የለም፡፡ እውነታን ሆን ብሎ የሚያድበሰብስና ግልፅ ወገንተኝነት የተንፀባረቀበት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ሪፖርት ፈፅሞ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ የሚፈይደው ነገር አይኖርም፡፡

የኢትዮጵያ በሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት
ነሐሴ 21 ቀን 1997 ዓ.ም.
አዲስ አበባ፣